# ስለአቶ ስዬ አብርሃ ከእስር መለቀቅ
# የአቋም መግለጫ

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ
የትግራይ ተወላጆች አስተባባሪ ኮሚቴ
<u>ሐምሌ 7 ቀን 1999 ዓ.ም</u>

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የምንኖር የትግራይ ተወላጆች የአገራችንን የፍትህ ሥርዓት አፈፃፀም በማስመልከት በተለይም የኢፌዲሪን ሕገመንግሥት ከማክበርና ከማስከበር ብሎም የአገሪቱን ሕግ ከማስፈፀም አኳያ በአቶ ስዬ አብርሃና በቤተሰቦቻቸው ላይ በጳኝነት አለመሟላት እየተመካኘ የተፈፀመውን የተራዘመና የተጓተተ ኢፍትሃዊ አያያዝና አካሄድ እንደመነሻ ነጥብ በመያዝ፣ በአካልና በቴሌኮንፍረንስ ሰፋፊ ውይይቶችን በማካሄድ፣ ለኢፌዲሪ መንግሥት አስፈፃሚ አካላት፣ ለአገራችን የሕግ መወሰኛና የሕግ አውጭ ምክር ቤቶች፣ እንዲሁም ለኢፌዲሪ ጠቅላይ ፍርድቤትና የሕግ አስፈፃሚ አካላት በደብዳቤና በአካል የአቤቱታና የተቃውሞ ድምፃችንን ስናሰማ መቆየታችን የሚታወስ ነው::

ሐምሌ 3 ቀን 1999 ዓ.ም ያስቻለው የአገራችን የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድቤት 'ለወንድማቸው ሕገ-ወጥ ጥቅም ለማስገኘት ጥረት አድርገዋል' በሚል በአቶ ስዬ አብርሃ ላይ ባስተላለፈው የቅጣት ውሳኔ፣ በቁጥጥር ሥር ከዋሉበት ቀን ጀምሮ በሚታሰብ የአምስት ዓመት እስራትና 500 ብር መቀጫ ማስተላለፉ ታውቋል:: በዚህም ፍርድ መሠረት ለስድስት ዓመት ከሁለት ወር በእሳፊ ስለታሰሩ በፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ በነፃ ከእስር እንዲለቀቁ ተደርጓል::

በአቶ ስዬ አብርሃና በቤተሰቦቻቸው ከእስር መለቀቅ በአሜሪካና በካናዳ የምንኖር ፍትህ ወዳድ ኢትዮጵያውያን ወገኖች ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማን ስንገልፅ፣ ለአቶ ስዬ አብርሃ ለቤተሰቦቻቸውና ፍትህ ለተጠማው ወገናችን በሙሉ የእንኳን ደስ ያላችሁ መልእክታችን ይድረሳችሁ::

ፍትህ የሰፈነበትና የሕግ የበላይነት የተረጋገጠበት ሥርዓት ለሕዝቦች መብት መከበርና ለአገር ሰላም ልማትና ዕድገት ዋስትና እንደመሆኑ፣ የአገራችን የሕግ አስፈፃሚ አካላት ብሎም የኢፌዲሪ መንግሥት ከሕዝብ የተነሳውን የፍትህ መነፈግ ብሶት በማዳመጥ፣ ከተጓተተና

ከተንዛዛ የፍትህ አፈፃፀም በኋላ በመጨረሻው ሰዓት ላይ በተገቢው ዳኛ በመሰየምና በአጫጭር ቀጠሮዎች በማስቻል፣ የአቶ ስዬና የቤተሰቦቻቸው ጉዳይ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ እልባት እንዲያገኝ በመደረጉ፣ በተለይም ለአገራችን የሕግ አስፈፃሚ አካላት በአጠቃላይም ለኢፌዲሪ መንግሥት ስለፍትህ አክብሮታችንን እንገልፃለን።

ሆኖም ግን፣ በአቶ ስዬ አብርሃ ላይ የተላለፈው የጥፋተኝነትና የቅጣት ውሳኔ ምንም እንኳን በፍርድ ቤት የተላለፈ ውሳኔ በመሆኑ ብቻ ብናከብረውም፣ በበቂ ማስረጃ ያልተደገፈና በስም-በለው 'ለወንድማቸው ሕገ-ወጥ ጥቅም ለማስገኘት አስነግረዋል' በሚል ከአሉባልታ ባልዘለለ ተራ ውንጀላ ብቻ የፖለቲካና ወታደራዊ ተክለ-ሰውነታቸውን ክብራቸውንና ንፅህናቸውን ለማጉደፍ በማለም፣ ብሎም ከስድስት ዓመት በላይ አለአግባብ የታሰሩበትን ጊዜ ለማካካስ የተሰራ በሚመስል የስሌት የቅጣት ውሳኔ መስጠቱ በጣሙኑ አሳዝኖናል።

ደግመን ደጋግመን በዜግነታችን የምናስምርበት አብይ ነጥብ፣ የኢፌዲሪ መንግሥት ተቀዳሚ ተግባርና ግዴታው ስለዜጎች መብትና ስለአገራችን ጥቅሞችና ሉዓላዊነት መከበር ዘብ የቆመውን የሕጎች ሁሉ የበላይ የሆነውን የአገራችንን ሕገመንግሥት በማክበርና በማስከበር፣ ፍትህ ሰፍኖ የሕግ የበላይነት ተረጋግጦ ሕዝቦች ከእርስ በርስ አተካራ ግጭትና ብሶት ተላቀው፣ ትኩረታቸው ስለልማትና ስለዕድገት ብቻ የሚሆንበትን ዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ማረጋገጥ ላይ አፅንዖት እንዲሰጥ አጥብቀን በመጠየቅ ነው።

የተከበራችሁ በአሜሪካና በካናዳ የምትኖሩ የትግራይ ተወላጆች፣ የአቶ ስዬ አብርሃንና የቤተሰቦቻቸውን ኢፍትሃዊ አያያዝና የሕግ አፈፃፀም በማስመልከት ምንም ዓይነት ልዩነት ሳያግደን በሕብረት የፍትህ አቤቱታና የተቃውሞ ድምፃችንን በማሰማት ያካሄድነውን እንቅስቃሴ በማስመልከት፣ የተከበሩ አቶ ስዬ አብርሃ አድናቆታቸውን በመግለፅ፣ "... ስለእኔና ስለቤተሰቦቼ መብት መከበር፣ በአጠቃላይም ስለሕግ ልዕልና መረጋገጥ ድምፃችሁን ያሰማችሁልን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን በሙሉ፣ በእራሴ በቤተሰቦቼና በወገኖቼ ስም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ..." በማለት መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

በሰሜን አሜሪካና በካናዳ የትግራይ ተወላጆች
አስተባባሪ ኮሚቴ
Email: justice4siye@Gmail.com